www.abyssinialaw.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፮
አዲስ አበባ ጥቅምት ፴ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 66
ADDIS ABABA 9th November 2009

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፷፰/፪ሺ፩

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ገፅ ፭ሺ፶፩

CONTENTS

Regulation No. 168/2009

Charities and Societies Council of Ministers Regulation ........................ Page 5051

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፷፰/፪ሺ፩

ስለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ምዝገባና አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፩/፪ሺ፩ አንቀጽ ፻፱ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፷፰/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩/ "አዋጅ" ማለት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፩/፪ሺ፩ ነው፤

፪/ "ኤጀንሲ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፬ መሠረት የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ነው፤

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህም ደንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

*Council of Ministers Regulation No. 168/2009*

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE REGISTRATION AND ADMINISTRATION OF CHARITIES AND SOCIETIES

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 109 of the Charities and Societies Proclamation No. 621/2009.

PART ONE

GENERAL

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Charities and Societies Council of Ministers Regulation No. 168/2009"

2. *Definition*

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Charities and Societies Proclamation No. 621/2009;

2/ "Agency" means the Charities and Societies Agency established under Article 4 of the Proclamation;

3/ The definitions provided in Article 2 of the Proclamation shall be applicable to this Regulation:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 8.25

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፬/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ነው፤

፭/ "የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ወይም የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፮/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት
## ስለምዝገባ

፫. ለመደበኛ ምዝገባ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩/ የምዝገባ ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ ፷፰ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፦

ሀ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሊሰራ ያሰበባቸውን ክልሎች ወይም የከተማ አስተዳደሮች ዝርዝር ወይም ማህበሩ ሊሰራ ያሰበባቸውን ክልሎች ወይም የከተማ አስተዳደሮች ዝርዝር እና የማህበሩ መሥራች አባላት መኖሪያ አድራሻ፤

ለ) ኤጀንሲው ባዘጋጀው ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ለመመራት የተሰጠ ስምምነት ወይም በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ መስራቾች የተፈረመ መተዳደሪያ ደንብ፤

ሐ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የገንዘብ ምንጭ ከመቶው ምን ያህሉ ከኢትዮጵያ ውስጥ እንደሆነ ወይም እንደሚሆን፤

መ) እንደነገሩ ሁኔታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የሥራ መሪዎች፣ መስራቾችና አባላት ስም፣ አድራሻ፣ ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃና ዜግነት፤

ሠ) ሊቋቋም የታሰበውን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ዓይነት፤

ረ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሊጠቀምበት የሚፈልገው ምልክት ካለ ይህንኑ፤ እና

ሰ) በኤጀንሲው የሚጠየቁ ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ እንደነገሩ ሁኔታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ መሥራቾች፣ ባለአደራዎች ወይም ተወካዮች የፈረሙበትና ማመልከቻው ውስጥ የተመለከቱት መረጃዎች እውነት ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የተሰጠበት መሆን ይኖርበታል።

4/ "state" means any state referred in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

5/ "city administration" means the Addis Ababa or Dire Dawa city administration;

6/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO
## REGISTRATION

3. *Application for Normal Registration*

1/ Without prejudice to the requirements prescribed under sub-article (3) and (4) of Article 68 of the Proclamation, an application for registration shall include the following information:

a) the list of regions or city administrations wherein the charity intends to operate or the list of regions or city administrations wherein the society intends to operate and residences of the founding members of the society;

b) declaration given to use model rules prepared by the Agency or rules signed by the founders of the charity or the society;

c) what percentage of its income is generated or will be generated from Ethiopian sources;

d) names, addresses, ages, educational status and nationalities of the founders, officers and members of the charity or society, as the case may be;

e) the legal nature of the charity or society;

f) symbol intended to be used by the charity or society, if any; and

g) other relevant information requested by the Agency.

2/ An application made under sub-article (1) of this Article shall be signed and attested by the founders, trustees or agents of the charity or the society, as the case may be.

www.abyssinialaw.com



፫/ ኤጀንሲው የፈቃድና ምዝገባ ጥያቄውን ውድቅ ካደረገ ምክንያቶችን ጨምሮ ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል። ማመልከቻው ውድቅ መደረጉ አመልካቹ በዚህ ደንብ መሠረት የከፈለው የአገልግሎት ክፍያ እንዲመለስለት አያደርግም።

፬/ ኤጀንሲው ምዝገባ የሚያካሂደው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን አግባብነት ያለው ክፍያ በማስከፈል ይሆናል።

፬. <u>የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች</u>

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፷፰ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የምዝገባ ማመልከቻ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል:-

ሀ) ድርጅቱ ለትግበራ ያዘጋጀው የፕሮጀክት ፕሮፖዛል፤

ለ) የድርጅቱ የሀገር ውስጥ ተወካይ ዝርዝር የግል መረጃ፤ እና

ሐ) ሌሎች ኤጀንሲው በመመሪያ የሚወስናቸው መረጃዎች።

፪/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት የድጋፍ ደብዳቤ ለመስጠት ሊከተላቸው የሚገባውን ዝርዝር መስፈርቶች ከኤጀንሲው ጋር በመመካከር ያወጣል።

፫/ ኤጀንሲው የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት ምዝገባን የሚያካሂደው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል ይሆናል።

፭. <u>የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ስያሜ</u>

የአመልካችን ወይም የተመዘገበን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስያሜ:-

፩/ ከሌላ አስቀድሞ ከተመዘገበ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስም ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተቀራራቢ ሲሆን፤

፪/ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ከሰፈሩት እውነተኛ ዓላማዎቹና ሥራዎቹ አንፃር ህብረተሰቡን ሊያሳስት የሚችል ሲሆን፤

፫/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ምንም ግንኙነት ሳይኖረው በሆነ መልኩ ከመንግሥት ወይም ከማንኛውም የመንግስት አካል ወይም ከማናቸውም የሰዎች ስብስብ ወይም ግለሰብ ወይም የንግድ ድርጅት ጋር ግንኙነት እለው የሚያስኝ ግምት የሚፈጥር ሲሆን ፤

ኤጀንሲው ስያሜው እንዲቀየር ያደርጋል።

3/ When the Agency denies the application for registration it shall notify the applicant in writing by stating the reasons for the denial. A denial of the application may not entitle to the refund of fees paid under this Regulation.

4/ The Agency shall effect registration upon receiving the appropriate fees prescribed in the Schedule attached hereto.

4. *Foreign Charities*

1/ Without prejudice to sub-article (4) of Article 68 of the Proclamation and sub-article (1) of Article 3 of this Regulation, the application of foreign charities shall include:

a) a project proposal prepared for implementation;

b) detailed information about its country representative, and

c) other information as may be required by directives of the Agency.

2/ The Ministry of Foreign Affairs shall, in consultation with the Agency, determine the criteria to be used for the issuance of its letters of recommendation to foreign charities.

3/ The Agency shall effect registration of a foreign charity upon receiving fees prescribed in the Schedule attached hereto.

5. *Name of Charities and Societies*

The Agency shall require the change of a name of an applicant or a registered charity or society where such name:

1/ is the same as or is similar to that of any other charity or society registered earlier;

2/ is likely to mislead the public as to the true nature of the purposes specified in its rules and the activities which the charity or society carries on;

3/ is likely to give the impression that the charity or society is connected in some way with the Government or any government organ, or with any other body of persons or any individual or business, when it is not so connected.

www.abyssinialaw.com



፮. <u>መተዳደሪያ ደንብ ስለሚይዛቸው ዝርዝሮች</u>

፩/ የማንኛውም በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተዳደሪያ ደንብ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፦

ሀ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን ስያሜ፣ አድራሻና ዓላማ፤

ለ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን አደረጃጀት፤

ሐ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የበጀት ዓመት፤

መ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም፤

ሠ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የሥራ መሪዎች የሚመረጡበት ወይም የሚቀጠሩበት ሥርዓት፣ ሥልጣንና ተግባራቸው እንዲሁም የሥራ ዘመናቸው፤

ረ) አባላት ወይም የሥራ መሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ አባልነታቸው ወይም የሥራ መሪነታቸው ስለሚቀርበት ሁኔታ፤

ሰ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የበላይ አካልና አመራር አካላት የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት፤

ሸ) ማህበር ከሆነ አባላትን የሚቀበልበትና የሚያሰናብትበት ሥርዓት እና ስለ አባላቱ መብትና ግዴታዎች እንዲሁም ስለሚያደርጉት መዋጮ፤

ቀ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ስለሚሻሻልበት ሥነ ሥርዓት፤

በ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የገቢ ምንጮች፤

ተ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ አርማ ወይም ምልክት ካለው ይህንኑ፤

ቸ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሲፈርስ ተፈጻሚ ስለሚሆነው ሥነ-ሥርዓት፤ እና

ኀ) ሌሎች በኤጀንሲው መመሪያ የሚወሰኑ ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ከማህበሩ ባህሪ አንጻር አግባብነት ያላቸው ጉዳዮች።

፪/ ኤጀንሲው ባዘጋጀው ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ሳይሆን የራሱን መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅቶ የሚቀርብ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ለምዝገባ ከሚጠየቀው ክፍያ በተጨማሪ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን መተዳደሪያ ደንብ ማስገምገሚያ ክፍያ ይከፍላል።

6. *Contents of Rules*

1/ Rules of any charity or society shall contain the following particulars:

a) name, address and objectives of the charity or society;

b) organizational structure of the charity or society;

c) budget year of the charity or society;

d) the administration and utilization of the financial resources of the charity or society;

e) procedure through which the officers of the charity or society are elected or employed and their powers and functions and their terms of office;

f) the conditions on which membership or tenure of officers of the charity or society ceases;

g) meeting and decision making procedures of the governing body and executive organs of the charity or society;

h) if it is a society, the procedure through which it receives or discharges its members, the rights and duties of members as well as membership contribution;

i) procedure through which the rules of the charity or society are amended;

j) sources of income of the charity or society;

k) the logo or symbol of the charity or society, if any;

l) procedure applied when the charity or society is dissolved; and

m) other relevant information prescribed by directives of the Agency in light of the nature of the charity or society.

2/ A charity or society intending to utilize rules prepared by itself instead of the model rules prepared by the Agency shall, in addition to registration fee, pay the fee prescribed for vetting rules in the Schedule attached hereto.

፯. ወዲያው ስለሚፈፀም ምዝገባ

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ የተመለከተው እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም የኤጀንሲውን ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ለመጠቀም ፈቃደኛ የሆነ፣ የፕሮጀክት መግለጫ ማቅረብ የማይጠበቅበትና ሕብረት ያልሆነ የኢትዮጵያ ማህበር ወዲያውኑ ይመዘገባል፡፡

፪/ ወዲያውኑ መመዝገብ የሚችሉ የኢትዮጵያ ማህበራት የሚገለገሉበትን ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦችን ኤጀንሲው ያዘጋጃል፡፡

፫/ ወዲያውኑ የተመዘገበ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ መልኩ መመዝገብ ያልነበረበት ሆኖ ሲገኝ፡-

ሀ) መደበኛ ምዝገባ ለማድረግ የሚጠየቁ መስፈርቶችን እንዲያሟላ ከተደረገ በኋላ የተመዘገበበት ቀን ሳይቀየር በአዋጁ አንቀጽ ፷፰ መሠረት እንደተመዘገበ ይቆጠራል፤

ለ) ለመደበኛ ምዝገባ የሚያስፈልገውን ቀሪ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ቢኖርም ኤጀንሲው በአዋጁ አንቀጽ ፺፪ የተሰጠውን ሥልጣን በተጠቀሰው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ላይ ከመፈጸም አያግደውም፡፡

፭/ ኤጀንሲው ወዲያውኑ ስለሚመዘገቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፰. ህብረት ስለመመስረት

፩/ ማናቸውም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት የጋራ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚፈጠር ህብረት እንደ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ሕብረት ለመመስረት የሚፈልጉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት የእያንዳንዱ ድርጅት ወይም ማህበር የበላይ አካል ወይም በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት ስልጣን የተሰጠው አካል ውሳኔውን ያስተላለፈበትን ቃለ-ጉባኤ ማቅረብና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ለመደበኛ ምዝገባ የተመለከተውን ክፍያ መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡

፱. ምዝገባን በማስመልከት የሚቀርቡ ተቃውሞዎች

ማንኛውም ሰው አንድ አመልካች በበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት መመዝገቡ ወይም የስም፣ አርማ ወይም ምልክቶች ለውጥ ማድረጉ የሚጎዳው ሲሆን ምዝገባውን ወይም በመዝገብ ውስጥ የሚሰፍረውን ማናቸውንም ዝርዝር ሊቃወም ይችላል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ተቃውሞ የሚቀርበውና የሚወሰነው ኤጀንሲው በሚዘረጋው ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

7. *Immediate Registration*

1/ Without prejudice to Article 3 of this Regulation, any Ethiopian society that is willing to use model rules prepared by the Agency, is not expected to submit a project profile and is not a consortium may be registered immediately.

2/ Model rules for the use of Ethiopian societies that might be registered immediately shall be prepared by the Agency.

3/ Where it is revealed that a charity or society which is not entitled to register immediately is so registered:

a) is shall, upon requiring it to fulfill the criteria for normal registration, be considered to have registered under Article 68 of the Proclamation without altering the date of registration; and

b) it shall pay the remaining balance of the required for normal registration.

4/ Notwithstanding sub-article (3) of this Article, the Agency shall not be prevented from exercising its powers under Article 92 of the Proclamation.

5/ The Agency may issue directives on particulars of charities and societies to be registered immediately.

8. *Formation of a Consortium*

1/ Any consortium formed by two or more charities or societies in order to achieve their common objectives shall be registered as a charity or society.

2/ Charities or societies applying to register a consortium shall produce the minutes showing the decision of the governing body of each charity or society or an organ given the power, under its rules, to form a consortium and shall pay fees prescribed for normal registration in the Schedule attached hereto.

9. *Objections to Registration*

Any person who may be affected by the registration of an applicant as a charity or society or by any change or amendment in name, logo or symbol may object to such registration or entry in the register. Such objection shall be made and dealt with in accordance with procedures established by the Agency.

www.abyssinialaw.com



፲. በድጋሚ ስለሚደረግ ምዝገባ

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት የተመዘገቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ያለምንም ክፍያ ኤጀንሲው በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በድጋሚ ይመዘገባሉ፡፡ ድጋሚ ምዝገባ የሚካሄድበት ዝርዝር በኤጀንሲው ይወሰናል፡፡

፪/ የድጋሚ ምዝገባ ውጤት ተግባራዊ የሚሆነው ድጋሚ ምዝገባው በተጠናቀቀበት ጊዜ ሳይሆን አዋጁ ከፀናበት ጊዜ ከአንድ ዓመት በኋላ ይሆናል፡፡

፲፩. ምልክቶችን ስለማስመዝገብ

፩/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሊጠቀምበት የወሰነውን አርማ ወይም ምልክት በጥቅም ላይ ከማዋሉ በፊት ለኤጀንሲው ማቅረብና ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ አርማ ወይም ምልክት ለማስመዝገብ የሚቀርበው ማመልከቻ የአርማውን ወይም የምልክቱን ቅጂ እንዲሁም አላማ፣ ቅርጽ፣ ይዘት፣ ቀለምና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝሮችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

፫/ ለምዝገባ የቀረበው አርማ ወይም ምልክት ተቀባይነት ያለው ከሆነ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

፬/ የአርማ ወይም ምልክት ምዝገባ ጥያቄውን ኤጀንሲው ካልተቀበለው ምክንያቶችን ጨምሮ ማመልከቻው ተቀባይነት አለማግኘቱን ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፭/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ የተደነገገው ከአስፈላጊ ማስተካከያ ጋር ለአርማና ምልክቶች ማሻሻልና መለወጥ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፲፪. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አደራ ጠባቂዎች

፩/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት እንደተመሰረተ የሚቆጠረው የድርጅቱ መሥራች ወይም እርሱ የወከለው ሰው ወይም ኤጀንሲው በአዋጁ መሰረት የአደራ ጠባቂ በሚሾምበት እና የተሾመው አደራ ጠባቂ በሹመቱ ተስማምቶ በተቀበለበት ቀን ነው፡፡

*10. Re-registration*

1/ Without prejudice to Article 3 of this Regulation, charities and societies registered prior to the effective date of the Proclamation shall be registered without payment of any fees in accordance with the schedule set by the Agency. Particulars shall be determined by the Agency.

2/ The effects of re-registration shall commence only a year after the effective date of the Proclamation and not immediately after re-registration.

*11. Registration of Symbols*

1/ Where a charity or society decides to use any logo or symbol, it shall, prior to any such use, present the logo or symbol to the Agency for registration.

2/ An application for registration shall be accompanied by a reproduction of and a description of the objectives, outline, color and other necessary details of the logo or symbol.

3/ If a logo or symbol presented for registration is acceptable, it shall be entered in the register of charities and societies upon payment of the fees prescribed in the Schedule attached hereto.

4/ When the Agency refuses an application for registration of a logo or symbol, it shall notify the applicant the decision and the reasons thereof in writing.

5/ The provisions of Article 16 of this Regulation shall, with the necessary adjustments, be applicable to changes and amendments of logos and symbols.

*12. Trustees of a Charitable Trust*

1/ A charitable trust shall be deemed to be formed on the day when the person constituting the trust or the person designated by him or the Agency has appointed a trustee in accordance with the Proclamation and the trustee acceptable the appointment.

www.abyssinialaw.com

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፷፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአደራ ጠባቂዎቹ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ድርጅቱን ለማስመዝገብ የምዝገባ ጥያቄ ሳያቀርቡ ከቀሩ ኤጀንሲው ከአደራ ጠባቂነት እንዲነሱና በሌላ እንዲተኩ ያደርጋል፡፡

፫/ ኤጀንሲው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከተቋቋመ በኋላ ባለው ሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የአደራ ጠባቂዎቹ የምዝገባ ማመልከቻ ያላቀረቡበት ምክንያት በቂ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን መስራች ወይም የሚመለከተውን የዘርፍ አስተዳዳሪ ሊያማክር ይችላል፡፡

፲፫. ስለአደራ ጠባቂዎችና ሦስተኛ ወገኖች ግንኙነት

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፷፭ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አደራ ጠባቂዎች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከማግኘታቸው በፊት በስጦታው ወይም ኑዛዜው ላይ የተመለከተውን ሀብት ባለይዞታነት ወይም ባለቤትነት ወደ አደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለማስተላለፍ ከሚያስፈልጉ ድርጊቶች በስተቀር ሦስተኛ ወገኖችን የሚያካትቱ ማናቸውንም ሕጋዊ ድርጊቶች ማከናወን አይችሉም፡፡

፪/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተላለፉ የአደራ ጠባቂዎች ከአደራ ጠባቂነት እንዲነሱና በሌላ እንዲተኩ ይደረጋል፡፡

፫/ የአደራ ጠባቂዎቹ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተላልፈው የፈጸሙት ድርጊት በአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ላይ ባደረሰው ጉዳት መጠን በአንድነት እና በነጠላ ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ የአደራ ጠባቂዎች ለሚፈጽሙት ድርጊት የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ኃላፊነት አይኖርበትም፡፡

፲፬. ፈቃድ ስለማሳደስ

፩/ ፈቃድ ለማሳደስ ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዓመታዊ የሥራ ክንውንና የኦዲት ሪፖርቶች ጋር የሚቀርብ ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ ፸፮ የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፦

ሀ) የሦስት ቀጣይ ዓመታት የበጀት ዕቀድ፤

ለ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ከሚመለከተው የመንግሥት አስፈጻሚ አካል ጋር የገባው የፕሮጀክት ስምምነት ካለ ይህንኑ፤

ሐ) ሌሎች ኤጀንሲው የሚጠይቃቸው ሰነዶች፡፡

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article (3) of Article 64 of the Proclamation, trusteeship of the trustees who fail to apply for registration of the charitable trust within three months of constitution of the charitable trust shall be revoked and a new trustee shall be appointed by the Agency.

3/ To decide whether the failure of the trustees to register within three months of the formation of the charitable trust is due to a justifiable cause or not, the Agency may consult with the person constituting the trust or the sector administrator.

*13. Relationship between Trustees and Third Parties*

1/ Without prejudice to the provisions of sub-article (3) of Article 65 of the Proclamation, trustees may not perform any acts involving third parties before acquiring a certificate of registration except the acts necessary for transferring the assets mentioned in the donation or will to the possession or ownership of the charitable trust.

2/ Trustees who contravene sub-article (1) of this Article shall be removed from the trusteeship and replaced by other trustees.

3/ Trustees shall be jointly and severally be liable for any damage caused to the charitable trust due to their acts committed in contravention of sub-article (1) of this Article.

4/ A charitable trust may not be liable for the acts of trustees committed in contravention of sub-article (1) of this Article.

*14. Renewal of License*

1/ Without prejudice to the requirements stipulated under Article 76 of the Proclamation, an application for the renewal of a license which shall be made concurrent with the annual activity and audit reports of a charity or society shall include the following information:

a) a financial plan of three subsequent budget years.

b) project agreement that the charity concluded with the concerned government bodies, if any; and

c) other documents as may be requested by the Agency.

www.abyssinialaw.com


፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈቃድን ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሥራ መሪ የተፈረመና ማመልከቻው ውስጥ የተመለከቱት መረጃዎች እውነት ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የተሰጠበት መሆን ይኖርበታል። ለዕድሳት የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው ይሆናል።

፫/ ኤጀንሲው የዕድሳት ጥያቄን ውድቅ ካደረገ ምክንያቶችን ጨምሮ ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

፬/ ኤጀንሲው የዕድሳት ጥያቄውን አስመልክቶ በመፍቀድም ሆነ በመከልከል የሚሰጠው ውሳኔ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ ውስጥ ይመዘገባል።

፲፭. ሕዝባዊ መዋጮ እና የበጎ አድራጎት ኮሚቴ

፩/ በአዋጁ መሰረት ሕዝባዊ መዋጮ ለማካሄድ ወይም የበጎ አድራጎት ኮሚቴን ለማፀደቅ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይገባዋል፦

(ሀ) ሕዝባዊ መዋጮ የሚደረግለት ወይም ኮሚቴ የሚቋቋምለት የበጎ አድራጎት ዓላማ፤

(ለ) ህዝባዊ መዋጮው የሚካሄድበት ወይም የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ሥራውን የሚሰራበት ቦታ ወይም የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት ቀን፤

(ሐ) ሕዝባዊ መዋጮው የሚካሄድበት ወይም የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ሥራውን የሚያካሂድበት ዘዴ፤

(መ) ሕዝባዊ መዋጮውን በበላይነት የሚመራው የሥራ መሪ ወይም ግለሰብ የሚመለከት መረጃ፤ ወይም የኮሚቴው የስራ መሪዎችና አባላት ዝርዝር መረጃ፤

(ሠ) ኤጀንሲው በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች መረጃዎች።

፪/ በህዝባዊው መዋጮ ወይም በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የሚሰበሰበው ሀብት ከአገር ውጭ ላለ የበጎ አድራጎት ተግባር ሊውል የሚችልበት ሁኔታ ሲኖር ሕዝባዊ መዋጮው ወይም በጎ አድራጎት ኮሚቴው ያለ ኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ይሁንታ ሊፈቀድ አይችልም።

2/ An application for the renewal of a license under sub-article (1)of this Article shall be signed and attested by the chief executive officer of the charity or society. The fees to be paid for renewal shall be as prescribed in the Schedule attached hereto.

3/ Where the Agency denies an application for the renewal of a license it shall inform the applicant in writing by stating the reasons for such denial.

4/ The decision of the Agency for granting or denying of an application for renewal shall be entered in the register of charities and societies.

15. *Public Collections and Charitable Committees*

1/ An application presented for public collection or approval of a charitable committee in accordance with the Proclamation shall include the following information:

a) the charitable purposes for which the public collection is to be conducted or for which the committee is constituted;

b) the place or places in which the public collection is to be conducted or the committee will operate and the date on which it will begin and end;

c) the method through which the public collection will be conducted or the committee will conduct its work;

d) information about the officer or the person who will supervise or direct the public collection or the officers or members of the committee; and

e) such other particulars as may be determined by directives of the Agency.

2/ The Agency shall not authorize a public collection or charitable committee without an explicit approval of the Director General of the Agency where any of the funds collected might be applied to charitable purposes outside of Ethiopia.

፲፮. <u>ስያሜን፣ የሥራ ቦታን ወይም መተዳደሪያ ደንብን ስለመለወጥ ወይም ስለማሻሻል</u>

፩/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በአዋጁ አንቀጽ ፸፫ መሠረት ስያሜውን ከለወጠ ወይም መተዳደሪያ ደንቡን ካሻሻለ ለውጡን ወይም ማሻሻያውን በሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት ለኤጀንሲው ማቅረብና ማስመዘገብ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በአዋጁ አንቀጽ ፸፫ መሠረት የሥራ ቦታውን ከለወጠ ለውጡን በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ወስጥ ለኤጀንሲው በጽሑፍ በማቅረብ ማስመዝገብ ይኖርበታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለማስመዝገብ የሚቀርበው ጥያቄ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የበላይ አካል ውሳኔ ቃለ ጉባኤ እና ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል የተፈለገው ስያሜ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ቅጂ መያዝ ይኖርበታል፡፡

፬/ የስያሜን ወይም የመተዳደሪያ ደንብን ማሻሻያ በኤጀንሲው ለማስመዝገብ የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው ይሆናል፡፡

፭/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ እንዲመዘገብለት የጠየቀው የስያሜ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ሕግ ያልተከለከለ ከሆነ ለውጡ ወይም ማሻሻያው ተመዝግቦ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ እንዲሰፍር ይደረጋል፡፡

፮/ ኤጀንሲው የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያን ሲመዘግብ የተሻሻለውን ደንብ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ይሰጣል፡፡

፯/ ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ እንዲመዘገብለት ያቀረበውን የስያሜ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ጥያቄ ካልተቀበለው ምክንያቶችን ጨምሮ ማመልከቻው ተቀባይነት አለማግኘቱን ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፲፯. <u>ስለመዋሐድና መከፋፈል</u>

፩/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ለመዋሀድ ወይም ለመከፋፈል ሲወስን ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር ጉዳዩን ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡-

16. *Change or Amendment of Name, Place of Work or Rules*

1/ If a charity or society changes its name or amends its rules in accordance with Article 73 of the Proclamation, it shall submit the change or amendment to the Agency for registration prior to the implementation of such change or amendment.

2/ If a charity or society changes its place of work in accordance with Article 73 of the Proclamation, it shall submit the change to the Agency for registration within fifteen working days of such change.

3/ An application for registration under sub-article (1) of this Article shall include a minute of the decision of the governing body of the charity or society and a copy of the changed or amended name or rules.

4/ The fees to be paid for registration of change or amendment of name or rules shall be as prescribed in the Schedule attached hereto.

5/ If the proposed change or amendments of name or rules of a charity or society is not prohibited by the Proclamation or by this Regulation or by any other law, the said change or amendment shall be entered in the register of charities and societies.

6/ The Agency shall, upon registration, supply the charity or society a copy of the registered amended rules.

7/ When the Agency refuses an application for registration of change of name or amendments of rules of a charity or society, it shall notify the applicant in writing the decision and the reason thereof.

17. *Merger and Division*

1/ Where a charity or a society decides to merge or divide, it shall present the following documents to the Agency:

(ሀ) አግባብነት ባለው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ አካል የመዋሐድ ወይም የመከፋፈል ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑን የሚያሳይ መስረጃ፤

(ለ) የተከፋፈሉትን ወይም የተዋሃዱትን የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ዝርዝር፤

(ሐ) ስለሚተላለፉት መብትና ግዴታዎች መጠን አግባብነት ባለው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ አካል የተደረገ ስምምነት፤

(መ) ውሳኔው መከፋፈል ከሆነ የንብረት ክፍፍሉ አፈጻፀም፤ እና

(ሠ) ሌሎች ኤጀንሲው የሚጠይቃቸው ዝርዝሮች፡፡

፪/ ኤጀንሲው መዋሐድና መከፋፈልን በሚመለከት ቀደም ሲል ተደርጎ የነበረው ምዝገባ በአዲሱ ሁኔታ መሠረት እንዲስተካከልና በጋዜጣ እንዲታተም የሚያደርገው የመዋሐድና የመከፋፈል ሂደትና ውሳኔ ተገቢነት ባላቸው ሕግጋትና መተዳደሪያ ደንቦች መከናወናቸውን አረጋግጦና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን የመደበኛ ምዝገባ ክፍያ በማስከፈል ይሆናል፡፡

፲፰. ስለመቀየር

፩/ ማናቸውም በኢትዮጵያ ውስጥ በአዋጁ መሠረት ፈቃድ አግኝቶ የተመዘገበ የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በበላይ አካሉ ውሣኔ ወደ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ሊቀየርና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሊያገኝ ይችላል፡፡

፪/ ማንኛውም የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወደ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ሲለወጥ በባለቤትነቱ ስር ያለን ከውጭ ምንጭ የተገኘን ሀብት ለተለወጠው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሊያስተላልፍ አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሰረት ወደ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ለመለወጥ ያመለከተ የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የነበረው ከውጭ ምንጭ የተገኘን ሀብት በድርጅቱ የበላይ አካል ወይም በኤጀንሲው ውሳኔ ተመሳሳይ ዓላማ ላለው የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ይተላለፋል፡፡

a) a document that shows the decision of the competent organ of the charity or society to merger or divide;

b) the list of the divided or merged charities or societies;

c) the decision of the competent organ of the charity or society as to the right and obligations to be transferred;

d) in the case of division, the procedures for partitioning of property; and

e) such other particulars as may be required by the Agency.

2/ The Agency shall enter the effects of a division or merger and have the same published only after verifying that the merger or division has been conducted in compliance with the relevant laws and rules and upon receiving the fees prescribed in the Schedule attached hereto for normal registration.

*18. Conversion*

1/ Any foreign charity registered in Ethiopia in accordance with the Proclamation or Ethiopian residents charity or society may be converted into an Ethiopian charity or society by the decision of its competent organ and acquire a certificate registration.

2/ A foreign charity or Ethiopian residents charity or society that applies to be converted to Ethiopian charity or society shall not transfer the assets that are from foreign sources to the converted charity or society.

3/ Any foreign charity or Ethiopian residents charity or society that applies for conversion in accordance with sub-article (1) of this Article shall, by virtue of its competent organ's or the Agency's decision, transfer its assets from foreign sources to a foreign charity or Ethiopian residents charity or society with similar purposes.

www.abyssinialaw.com

፬/ ማናቸውም በክልል የተመዘገበ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከተመዘገበበት ክልል በተጨማሪ በሌላ ክልል ውስጥ መሥራት ወይም አባላትን ማስገባት ከፈለገ ለኤጀንሲው በማመልከት በዚህ ደንብ መሠረት መመዝገብ ይችላል፡፡

፲፱. በጋዜጣ ስለማሳተም

፩/ ኤጀንሲው የተመዘገቡ ፣ የታገዱ፣ የተሰረዙ እና የፈረሱ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን እና ማህበራትን ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ በጋዜጣ ያወጣል፡፡

፪/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ለኤጀንሲው አቅርቦ የሚያስመዘግበውን የስም ለውጥ ወይም ማሻሻያ ኤጀንሲው ለውጡ ወይም ማሻሻያው በተመዘገበበት ወቅት በጋዜጣ ማውጣት አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም ለምዝገባ ያመለከተ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከምዝገባ ክፍያ በተጨማሪ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን የጋዜጣ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረተ በጋዜጣ ለማውጣት አመልካቹ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ ይከፍላል፡፡

፭/ የታገዱ ፣ የተሰረዙ እና የፈረሱ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን እና ማህበራትን ዝርዝር በጋዜጣ ለማውጣት የሚያስፈልገውን የማሳተሚያ ወጪ ኤጀንሲው ይሸፍናል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ጉዳዮች ኤጀንሲው በሚወስነው ማንኛውም ጋዜጣ ያወጣል ወይም እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ሪፖርቶችና መረጃዎች

፳. ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫ

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፸፰ መሰረት የሚዘጋጅ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ የሚከተሉትን ዝርዝሮች ሊይዝ ይገባል፡-

(ሀ) በበጀት ዓመቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ የገቢና ወጪ ሂሳብ፤

(ለ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የገቢ ምንጭ በተለይም ከውጭ የተገኘ ገቢ እና የአስተዳደርና የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ ድርሻ ማብራሪያ፤

4/ Any charity or society registered by a state may apply to the Agency for registration in accordance with this Regulation, if it plans to operate in or to admit members from another state in addition to the state of its registration.

*19. Publication*

1/ The Agency shall publish in a gazette the list of registered, suspended, canceled and dissolved charities and societies at least once in three months.

2/ The Agency shall publish in a gazette any changes in the names of charities and societies at the time that it has approved such change.

3/ Any charity or society applying for registration shall pay publication fees prescribed in the Schedule attached hereto in addition to registration fees.

4/ The applicant shall pay the fees prescribed in the Schedule attached hereto for publication in accordance with sub-article (2) of this Article.

5/ The Agency shall bear the costs of publishing the list of charities and societies that have been suspended, canceled or dissolved.

6/ The Agency shall publish or cause the publication of any matter pursuant to this Article in any gazette.

## *PART THREE*
## *REPORTS AND COMMUNICATION*

20. Annual Statement of Accounts

1/ An annual statements of accounts of a charity or society prepared in accordance with Article 78 of the Proclamation shall include:

a) an income and expenditure account showing the income and expenditure of the charity or society during the financial year;

b) explanation of the source of the income specially in relation to income from foreign sources and the ratio of administrative and operational costs of the charity or society;

www.abyssinialaw.com

(ሐ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በአመቱ መጨረሻ ላይ ያለውን አጠቃላይ ሀብት፣ እዳ እና ካፒታል የሚያሳይ የሃብት ሚዛን መግለጫ፤

(መ) የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የዋለውን የሂሳብ አሰራር መግለጫ፤ እና

(ሠ) ሌሎች በኤጀንሲው መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝሮች፡፡

፪/ ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከማናቸውም ምንጭ የሚያገኙትን ገቢ እና የአስተዳደርና የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ ማስላትን የሚመለከቱ ዝርዝር መስፈርቶችን ያወጣል፡፡

፫/ ኤጀንሲው የአስተዳደራዊ ስራዎችን ለመለየት የሚያስችል መመሪያ የወጣል፡፡

፬/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሕዝባዊ መዋጮ ካካሄደ የሂሳብ መግለጫው ሕዝባዊ መዋጮውን በሚመለከት ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

፳፩. <u>ዓመታዊ የሂሣብ ምርመራ</u>

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፸፱ መሰረት የሚዘጋጅ ዓመታዊ የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት የሚከተሉትን ዝርዝሮች ሊጠቅስ ይገባል፦

(ሀ) የሂሳብ መዛግብቱና መግለጫው የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን የገንዘብ እንቅስቃሴ እና ያሉበትን ሁኔታ በሚገባ የሚያሳይ መሆኑን፤

(ለ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩን አጠቃላይ ሃብት መዛግብትን ጨምሮ የሂሳብና ሌሎች መዛግብትን በአግባቡ መያዙን፤

(ሐ) የሂሳብ መዛግብቱና መግለጫው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከውጭ የሚያገኘውን ገቢ ለይቶ በሚያሳይ መልኩ መቀመጡን፤

(መ) ኦዲተሩ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሌሎች ዝርዝሮች፤ እና

(ሠ) ሌሎች በኤጀንሲው መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝሮች፡፡

፪/ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሕዝባዊ መዋጮ ያካሄደ ከሆነ የኦዲት ሪፖርቱ በመዋጮው የተሰበሰበውን ገንዘብ በተገቢው የሂሳብ አያያዝ መያዙን ወይም መጠበቁን የሚያመለክት ዝርዝር ሊያካትት ይገባል፡፡

c) a balance sheet showing the assets, liabilities and capital of the charity or society at the end of the financial year;

d) an explanation of the accounting policies used to prepare the accounts; and

e) such other particulars as the Agency may prescribe by directives.

2/ The Agency shall issue specific guidelines on how to calculate the income and expenditure of charities and societies in relation to income from any sources and administrative and operational costs.

3/ The Agency shall issue directives to distinguish administrative activities.

4/ Where the charity or society has conducted public collections during the financial year the statement of accounts shall include detailed accounts regarding the public collections.

21. *Annual Audit of Accounts*

1/ An annual audit report of accounts of a charity or society prepared in accordance with Article 79 of the Proclamation shall state:

a) whether the accounting records and statements fairly show the financial transactions and state of affairs of the charity or society;

b) whether proper accounts and other records have been kept, including records of all charity or society;

c) whether the accounting records and statements allow to distinguish income from foreign sources of the charity or society;

d) other particulars that the auditor deems necessary; and

e) such other particulars as the Agency may prescribe by directives.

2/ Where the charity or society has conducted public collections during the financial year the audit report shall state whether the public collection has been carried out in accordance with financial criteria set by the Agency and whether proper accounts and records regarding the public collection have been kept.

፳፪. ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፹ መሰረት የሚዘጋጅ ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት የሚከተሉትን ዝርዝሮች ሊይዝ ይገባል፦

(ሀ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዓላማውን ለማሳካት የቀረፃቸው የረጅምና አጭር ጊዜ እንዲሁም ሲኖረው ዓመታዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ፤

(ለ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በበጀት ዓመቱ ያከናወናቸው ተግባራት ማጠቃለያና አጠቃላይ ግምገማ፤

(ሐ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚፈፅማቸው ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ዝርዝር፤

(መ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በወቅቱ ያለውን ሃብት ሊያውል ያቀደበት ዓላማ ማብራሪያና የአጭርና ረጅም ጊዜ ዕቅዱ፤

(ሠ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሕዝባዊ መዋጮና ገቢ ማስገኛ ስራዎችን ካከናወነ ይህን የሚያብራራ ራሱን የቻለ መግለጫ፤ እና

(ረ) ሌሎች በኤጀንሲው መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝሮች።

፪/ የኢትዮጵያ ሴቶች፣ ወጣቶች እና መሰል ብዙሃን ማህበራት የሥራ ክንውን ሪፖርት ለኤጀንሲው ለማቅረብ አይገደዱም።

፫/ በኤጀንሲው ግምት አሳማኝ ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር በጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዓላማውን የመፈፀም ተግባር በዓመቱ ምንም ያላከናወነ ከሆነ በኤጀንሲው የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤ ሆኖም በቀጣዩ ዓመትም ምንም ተግባር ካላከናወነ ፈቃዱ በኤጀንሲው ይሰረዛል።

፳፫. ገቢ ስለሚያስገኝ ሥራ

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፩፻፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የሚያዝ የሂሳብ መዝገብ የሚዘጋጀው የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የተጣለባቸው ግብር ከፋዮች ላይ ተፈፃሚ በሆነ ተቀባይነት ባለው የሂሳብ አያያዝ ደረጃ መሰረት መሆን ይኖርበታል።

22. *Annual Activity Reports*

1/ An annual activity report of a charity or society prepared in accordance with Article 80 of the Proclamation shall include:

a) the short and long term and where applicable the annual policy and strategy applied by the charity or society in pursuance of its objectives;

b) summary and review of the activities of the charity or society during the financial year;

c) commitments of the charity or society to on-going projects;

d) an explanation of the purposes for which the charity's or society's assets are currently utilized and an indication of its future long-term and short-term plans;

e) where applicable a separate description of the public collections and income generating activities of the charity or society; and

f) such other particulars as the Agency may prescribe by directives.

2/ Ethiopian women, youth and similar mass based societies may not be obliged to submit annual activity reports to the Agency.

3/ The Agency shall give written warning to charity or society that has not operated to accomplish its established objectives with in the year unless, in the opinion of the Agency, an acceptable justification is presented by the charity or society. However, the Agency shall cancel its license where the charity or society has not operated in the next year.

23. *Income Generating Acivities*

1/ The books of accounts referred to in sub-article (2) of Article 103 of the Proclamation shall be kept in accordance with proper accounting standards applicable to taxpayers who have the obligation to keep books of accounts.

www.abyssinialaw.com

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፺፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎቹን በተመለከተ የተለየ የሂሣብ መዛግብት ያልያዘ እንደሆነ ወይም የሂሳብ መዝገቡን በተገቢ ሁኔታ ያልያዘ እንደሆነ ኤጀንሲው ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ለመሰማራት የተሰጠውን ፈቃድ ሊያግድበት ወይም ሊሰርዝበት ይችላል።

፫/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርቶ ያገኘውን ገቢ ከዓላማው ውጭ አውሎ የተገኘ እንደሆነ ኤጀንሲው በአዋጁ አንቀጽ ፺፪ የተመለከተውን አግባብ ያለው እርምጃ ይወስዳል።

## ፳፬. ስብሰባን አለማሳወቅ

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፺፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ በአዋጁ አንቀጽ ፹፮ መሠረት የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ ከሰባት የሥራ ቀናት አስቀድሞ የስብሰባውን ጊዜና ቦታ ሳያሳውቅ የቀረ ማናቸውም ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ማህበር የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሰጥ አይችልም።

## ፳፭. የባንክ ሂሣብን ስለመክፈትና ስለማሣወቅ

፩/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የባንክ ሂሳብ ለመክፈት ለኤጀንሲው ማሳወቅና የድጋፍ ደብዳቤ ማግኘት ይኖርበታል።

፪/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ያሉትን የባንክ ሂሳቦች በአዋጁ አንቀጽ ፹፫ መሠረት ከሚከተሉት ዝርዝሮች ጋር ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለበት፦

ሀ) ያሉትን የባንክ ሂሳቦች ብዛት፣ ዓይነት እና የተከፈቱበት ባንክና የቅርንጫፍ ባንኩ ስም እና የባንክ ሂሳቦቹ መለያ ቁጥር፤

ለ) የባንክ ሂሳቡ በማን እንደሚንቀሳቀስ፤

ሐ) በየጊዜው የሚቀርብ የባንክ ሂሳብ መግለጫ፤

መ) ኤጀንሲው በመመሪያ የሚጠይቃቸውን ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች ።

2/ Without prejudice to the provisions of Article 92 of the Proclamation the Agency may suspend or withdraw its approval for income generating activities where the charity or society has failed to keep separate books of account for its income generating activities or has failed to keep proper books of accounts.

3/ The Agency shall take the appropriate measures in accordance with Article 92 of the Proclamation where a charity or society is found to have utilized the proceeds of any income generating activity for the purpose other than its objectives.

## 24. *Failure to Notify Meetings*

1/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of Article 92 of the Proclamation any society or charitable society that fails to notify the Agency of the time and place of a meeting of its general assembly earlier than seven working days prior to such meeting as per Article 86 of the Proclamation may be given a written warning.

2/ A warning pursuant to sub-article (1) of this Article may not be given more than once.

## 25. *Notification of Bank Accounts*

1/ Any charity or society shall notify the Agency and acquire a supportive letter to open a bank account.

2/ Any charity or society shall notify to the Agency, as per Article 83 of the Proclamation, all the bank accounts of the charity or society with the following particulars.

a) the number of bank accounts, types of the accounts, the account numbers and the name of the bank where the accounts are opened with the respective branches;

b) the persons authorized to operate the accounts;

c) periodically issued bank statement; and

d) such other relevant particulars as the Agency may determine by directives.

www.abyssinialaw.com

፫/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የባንክ ሂሳብ ሊከፍት የሚችለው በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ ስም በኢትዮጵያ ውስጥ ባለ ባንክ ብቻ መሆን አለበት፡፡

፬/ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የባንክ ሒሳቡን ከዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርቱ ጋር ወይም ኤጀንሲው በጽሁፍ በሚጠይቀው በማናቸውም ጊዜ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡፡

፳፮. <u>አባላትንና የሥራ መሪዎችን የሚመለከቱ መረጃዎች</u>

፩/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር እንደሁኔታው አባላቱንና የሥራ መሪዎቹን ዝርዝር መረጃዎች መመዝገብና መጠበቅ እንዲሁም ለኤጀንሲው ማስተላለፍ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚያዘው መረጃ የሚከተሉትን ዝርዝሮች ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ) የአባላት፣ የሥራ መሪዎችንና የበላይ አካል አባላትን ሙሉ ስም፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ዜግነት፣ የመኖሪያ አድራሻና የትምህርት ደረጃ፤

ለ) የሥራ መሪዎችና የበላይ አካል አባላት የኃላፊነት ደረጃ ፣ ተግባርና ኃላፊነት እና የሥራ ቦታ፤ እና

ሐ) እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች በኤጀንሲው የሚወሰኑ መረጃዎች፡፡

፫/ ማንኛውም የበጎ አድጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ) ስር የተጠቀሱትን መረጃዎች እና እንደአግባብነቱ የአባላቱን ስም፣ ዕድሜና ፆታ ከዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት ጋር እንዲሁም ኤጀንሲው በሚጠይቅበት በማንኛውም ጊዜ ለኤጀንሲው ማሳውቅ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው ቢኖርም የኢትዮጵያ ብዙሃን ማህበራት የአባላታቸውን ብዛት ከማሳወቅ በስተቀር የአባላትን ዝርዝር መረጃዎች ማቅረብ አይጠበቅባቸውም፡፡

፭/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሥራ ወይም የበላይ አካል አባል ሲለውጥ ለውጡ በተደረገ በሰላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለበት፡፡

፮/ ኤጀንሲው ከማንኛውም በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር አባላቱን ወይም የሥራ መሪዎችን በሚመለከት የሚፈልገውን ዝርዝር መረጃ ሲጠይቅ በጽሁፍ መሆን አለበት፡፡

3/ Any charity or society may open an account only in its own name and with a bank situated in Ethiopia.

4/ Any charity or society shall present its bank account along with its annual activity reports or at any time as the Agency may require in writing.

26. *Information about Members and Officers*

1/ Any charity or society, as may be appropriate, shall record and keep particular regarding their members and officers and shall transmit the same to the Agency.

2/ A record of particulars in accordance with sub-article (1) of this Article shall include:

a) name, age, sex, nationality and address of members, officers and members of governing bodies;

b) officers' and members of governing bodies status, duties and responsibilities and place of work; and

c) such other particulars as may be required by the Agency.

3/ Any charity or society shall transmit to the Agency particulars under sub-article (2) (b) of this Article and, as appropriate, the name, age and sex of members together with its annual activity reports and whenever so requested by the Agency.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-article (3) of this Article, Ethiopian mass based societies may not be expected to report detailed particulars of members other than disclosing the number of their members.

5/ Any charity or society shall inform the Agency any changes in its officers or members of its governing body within thirty days of such change.

6/ When the Agency requires any particulars regarding members or officers from a charity or society, it shall request in writing.

www.abyssinialaw.com



፯/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በኤጀንሲው የተፈለገውን ዝርዝር መረጃ ኤጀንሲው በሚያስቀምጠው አግባብነት ባለው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

፰/ በአዋጁ አንቀጽ ፺፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን ያላሟላን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በጊዜ ገደብ የተወሰነ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት መረጃውን እንዲያሟላ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ማስጠንቀቂያ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሰጥ አይችልም፡፡

፳፯. <u>የጥቅም ግጭት</u>

፩/ የበጎ አድራጎት ድርጅትን ወይም ማህበርን ወክሎ ከሦስተኛ ወገን ጋር ግንኙነት በሚፈፀምበት ጊዜ በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ እና በእርሱመካከል የጥቅም ግጭት መከሰቱን ያወቀ የሥራ መሪ ወይም ተወካይ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የበላይ አካል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደ ተጠበቀ ሆኖ፤ ማንኛውም ሰው ወይም ኤጀንሲው በበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር እና የሥራ መሪ ወይም ተወካይ መካከል የጥቅም ግጭት መከሰቱን ካወቀ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡

፫/ የጥቅም ግጭት ስለመከሰቱ መረጃ የደረሰው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሚመለከተው አካል ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ጥቅም አንፃር ግጭት የተከሰተበት ግንኙነት የመቀጠል ወይም ያለመቀጠል ጉዳይ ላይ ይወሰናል፡፡ ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ጋር የጥቅም ግጭት ውስጥ የገባው የሥራ መሪ ወይም ተወካይ በዚህ ውሳኔ አሰጣጥ ሊሳተፍ አይችልም፡፡

7/ Any charity or society shall furnish any particulars as may be needed by the Agency within a reasonable period of time set by the Agency.

8/ Without prejudice to the provisions of Article 92 of the Proclamation, the Agency may give a written warning to a charity or society that has failed to fulfill the requirements of sub-article (2) of this Article to fulfill such requirement within a specified period. Such warning may not be given more than once.

27. *Conflict of Interest*

1/ Any officer or agent shall have the duty to disclose to his superior the existence of any conflict of interest between himself and the charity or society in making a transaction with a third party by representing the charity or society.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, when any person or the Agency becomes aware of the existence of a conflict of interest between a charity or society and its officer or agent, it may disclose the same to the charity or society.

3/ The appropriate body of a charity or society made aware of the existence of a conflict of interest shall determine, based on the best interest of the charity or society, whether the transaction that gave rise to the conflict should continue. The officer or agent whose interest is in conflict with that of the charity or society may not participate in such decision.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የተሰጡ ውሳኔዎች ተመዝግበው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት በሚያቀርብበት ጊዜ ለኤጀንሲው መቅረብ አለባቸው፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት የጥቅም ግጭት መፈጠሩን ያላሳወቀ የሥራ መሪ ወይም ተወካይ በአዋጁ አንቀጽ ፺ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

4/ Decisions made pursuant to sub-article (3) of this Article shall be recorded and reported to the Agency together with the annual activity report of the charity or society.

5/ Without prejudice to the provisions of Article 90 of the Proclamation, an officer or agent who has failed to disclose the existence of a conflict of interest in accordance with sub-article (1) of this Article shall be subject to a sanction prescribed under the rules of the charity or society.

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**፳፰. የምዝገባ የምስክር ወረቀትን በይፋ ስለማሳየትና ስለማስታወቂያ ሰሌዳ**

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፸፭ ድንጋጌን ያላከበረ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሚፈለገውን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲፈጽም ኤጀንሲው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሰጥ አይችልም፡፡

**፳፱. ስለኤጀንሲው ትዕዛዞች**

፩/ በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት ለበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ለማህበር በኤጀንሲው የሚሰጥ ማናቸውም ትእዛዝ በጽሑፍ ሆኖ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መፈፀም እንዳለበት መገለጽ ይኖርበታል፡፡

፪/ በኤጀንሲው ትእዛዝ የተሰጠው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በትእዛዙ መሠረት ስለመፈፀሙና የተፈፀመበትን ቀን ለኤጀንሲው በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፫/ የማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሥራ መሪ የአዋጁን፣ የዚህን ደንብ ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች በሚጥስበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ ጥፋቱን እስኪያርም ወይም በወንጀል ተከሶ ፍርድ እስኪያገኝ ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በሌላ እስኪተካ ድረስ በኤጀንሲው ከኃላፊነት ሊታገድ ይችላል፡፡

***28. Display of Certificate and Use of Advertisement Boards***

1/ The Agency may give a written warning to a charity or society that has failed to observe the provisions of Article 75 of the Proclamation and set a deadline to comply with requirements of the provisions.

2/ A warning pursuant to sub-article (1) of this Article may not be given more than once.

***29. Orders of the Agency***

1/ Any order of the Agency given to a charity or society pursuant to the Proclamation or this Regulation shall be made in writing and state the time limit for its execution.

2/ A charity or society given an order by the Agency shall notify the Agency its execution of the order and the date of execution.

3/ The Agency may suspend the officer of a charity or society where he contravenes the provisions of the Proclamation, this Regulation or the rules of the charity or society until he corrects his misconduct, or is sued and prosecuted in court of law or is replaced by another officer in accordance with the rules of the charity or society.

www.abyssinialaw.com



፬/ ኤጀንሲው በአዋጁ መሠረት ዕገዳ የተጣለበት የሥራ መሪ ወይም በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የዕገዳው ምክንያት የሆኑ ጥፋቶችን በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ማስተካከል እንደሚገባው በመግለጽ በጽሑፍ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

፴. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ቦርድ

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፯(፩) የተመለከተው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ቦርድ አባል የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ሆኖ እንደገና ለመሰየምም ገደብ አይኖርበትም፡፡

፪/ የቦርድ አባል ሲሞት፣ ሲለቅ ወይም ከኃላፊነት ሲነሳ የሥራ ዘመኑ እስከሚያበቃ ድረስ ተተክቶ የሚሠራ አዲስ አባል ይሰየማል፡፡

፫/ ቦርዱ ከቦርዱ አባላት ውጭ የሆነ በኤጀንሲው የሚመደብና የሚከተሉትን ተግባራት የሚያከናውን ፀሐፊ ይኖረዋል፦

ሀ) የቦርዱን የውስጥ ጉዳዮች ይመራል፤

ለ) ለቦርዱ የሚቀርቡትን ማመልከቻዎች ይቀበላል፤

ሐ) የቦርዱን ውሳኔ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤

መ) የቦርዱን ሰነዶች ይይዛል፤

ሠ) ሌሎች በቦርዱ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

፴፩. ቅጾችና ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦች

ኤጀንሲው በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች አስፈላጊ የሆኑ ቅፆችን እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦችን ያዘጋጃል፡፡

፴፪. የአገልግሎት ክፍያዎች

፩) ኤጀንሲው ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

፪) የፍትህ ሚኒስትሩ አግባብ ሆኖ ሲያገኘው ለማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ ደንብ መሠረት ለምዝገባ ወይም ለሌላ አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎችን በከፊል ወይም በሙሉ ቀሪ ሊያደርግ ይችላል፡፡

4/ The Agency shall give a written order to an officer or charity or society suspended in accordance with the Proclamation to rectify, within a specified time limit, the irregularities which caused the suspension.

30. *Charities and Societies Board*

1/ The tenure of a member of the Charities and Societies Board referred to in Article 7(1) of the Proclamation shall be for five years, and may be reappointed without any limit.

2/ Where a member of the Board dies, resigns or is removed, a new member shall be appointed to serve for the remaining term of the former member.

3/ The Board shall have a secretary appointed by the Agency outside of the Board members who shall:

a) look after the internal affairs of the Board;

b) receive applications to the Board;

c) transmit decisions of the Board to the concerned bodies;

d) keep the Board's documents; and

e) perform other functions as may be assigned to him by the Chairperson of the Board.

31. *Forms and Model Rules*

The Agency shall prepare forms that are necessary for the services it renders in accordance with the Proclamation and this Regulation and model rules of charities and societies.

32. *Fees*

1/ The amount of fees payable for the services rendered by the Agency shall be as prescribed in the Schedule attached hereto.

2/ The Minister of Justice may waive partly or totally registration or any other fees under this Regulation for any charity or society where he deems such waiver appropriate.

www.abyssinialaw.com



*33. Delegation of Power*

The Ministry of Justice may delegate to the Agency the power to register religious organizations given to it under sub-article (8) of Article 23 of Proclamation No. 471/2005.

*34. Power to Issue Directives*

The Agency may issue directives necessary for the proper implementation of this Regulation.

*35. Inapplicable Laws*

No regulations, directives or customary practice shall, in so far as they are inconsistent with this Regulation, be applicable with respect to matters provided for under this Regulation.

*36. Effective Date*

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

*Done at Addis Ababa, this 9th day of November, 2009.*

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

፴፫. ውክልና ስለመስጠት

የፍትህ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፰) የተሰጠውን የሃይማኖት ድርጅቶችን የመመዝገብ ሥልጣን በውክልና ለኤጀንሲው ሊሰጥ ይችላል ፡፡

፴፬. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ኤጀንሲው ለዚህ ደንብ አፈጻፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፴፭. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፴፮. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥቅምት ፴ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

www.abyssinialaw.com



## ሠንጠረዥ

## የአገልግሎት ክፍያዎች

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ ዓይነት | የክፍያ መጠን | |
|---|---|---|---|
| | | ብር | ዩ.ኤስ.ዲ. |
| ፩ | መደበኛ ምዝገባ | ፭፻ | |
| ፪ | የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ምዝገባ | | ፫፻ |
| ፫ | ወዲያውኑ ምዝገባ | ፬፻ | |
| ፬ | የአርማና ምልክት ምዝገባ | ፩፻ | |
| ፭ | የሥያሜና መተዳደሪያ ደንብ ለውጥና መሻሻል ምዝገባ | ፩፻ | |
| ፮ | ዕድሳት | ፬፻ | |
| ፯ | የተፈረሙና የተረጋገጡ የመተዳደሪያ ደንቦች | ፩፻ | |
| ፰ | ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎችና ሕዝባዊ መዋጮ ማስፈቀድ | ፩፻፶ | |
| ፱ | የደንበኞች መመሪያ | ፳ | |
| ፲ | የማመልከቻ ቅጽ | ፭ | |
| ፲፩ | የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎችን ማፀደቅ | ፪፻ | |
| ፲፪ | የሰነድ ትክክለኛ ቅጅ በገጽ | ፭ | |
| ፲፫ | የመተዳደሪያ ደንብ ማስገምገምያ | ፪፻ | |
| ፲፬ | ጋዜጣ ማሳተሚያ፤<br>ሀ) በምዝገባ ወቅት | የወቅቱ የማሳተሚያ ዋጋ ግማሽ | |
| | ለ) በስያሜ ለውጥ ወቅት | የወቅቱ የማሳተሚያ ዋጋ | |

## SCHEDULE

## FEES

| No. | Types of Service | Amount | |
|---|---|---|---|
| | | Birr | USD |
| 1 | Normal Registration | 500.00 | |
| 2 | Registration of foreign charities | | 300.00 |
| 3 | Immediate Registration | 400.00 | |
| 4 | Registration of symbols | 100.00 | |
| 5 | Change or amendment of name, place of work or rules | 100.00 | |
| 6 | Renewal | 400.00 | |
| 7 | Application to receive signed and sealed rules | 100.00 | |
| 8 | Application for income generating activities and public collections | 150.00 | |
| 9 | Customers' handbook | 20.00 | |
| 10 | Application form | 5.00 | |
| 11 | Approval of charitable committee | 200.00 | |
| 12 | For authenticated copy of each page of any document | 5.00 | |
| 13 | Vetting of rules | 200.00 | |
| 14 | Publication<br>a ) For Registration | Half of the current publication cost | |
| | b) For change of Name | current publication cost | |